Amharic Translation

## የ2018 የአለም ቴአትር ቀን የአረብ ሀገራት መልዕክት

## ማያ ዘቢብ ከሊባኖስ

## የቴአትር አዘጋጅ፣ ተዋናይ፣ ጸሐፌ-ተውኔት እና የዙካክ ቴአትር ድርጅት መስራች አባል

በየትኛውም የባዕድ እንቅስቃሴ ውስጥ የማይገኝ፣የሃሳብ ድግግሞሽ የማይስተዋልበት፣ለጋራ አላማ መሰባሰብን የሚጠይቅ የህይወት መቁጠሪያ የጊዜ ሰሌዳ ነው፡፡ ሰዎች የህይወት ልምዳቸውን ለመለዋወጥ ይሁነኝ ብለው በተመሳሳይ ወቅት እና ቦታ አንድነት የሚፈጥሩበት ቀላል የቡድን ክዋኔ ነው፡፡ ግለሰቦች ሃሳባቸውን ለማጋራት እና ነገን ለማቃናት የሚመክሩበት፤ሰብዓዊ አንድነትን የሚያበስሩበት፤በለሆሳስ አብሮነትን የሚያከሙበት፤ከልዩነት ይልቅ አንድነትን የሚፈልጉበት፤በነጠላ የሃሳብ መዋጮ የጋራ አለም የሚፈጠርበት ለእያንዳንዱ ሰው የሚቀርብ የክብር ግብዣ ነው፡፡ የቴአትር ጥበብ!!! በአንድ ውስን ቦታ የተፈጸመ ነጠላ ታሪክ ድንበሮችን አልፎ ሁለንተናዊ ስምምነትን ይፈጥራል፤የቴአትር ተዓምራዊ አቅሙ ይህ ነው፡፡ በውክልና ጥንትን ሁሌም አዲስ አድርጎ ማቆየት መቻሉን ነው ቴአትር የምንለው፡፡

አንዱ ሌላውን ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ፍርሃት የጎሪጥ ማየቱ አለም አቀፍ ባህል በሆነበት፤ ግለኝነት እና መገንጠል በልካችን የተሰፉ መደበኛ ሰዋዊ ባህሪያት ሆነው በነገሱበት ምድር፤ ቴአትር አንድ ላይ በመሆን የስሜት አንድነት፣ሰብዓዊ ህብረት የምንፈጥርበት፣ አሁናችንን የምናሳምርበት የፍቅር መከወኛ ጌጣችን ነው፡፡ለቅጽበታዊ ስጋዊ ደስታ ጊዜያችንን እንደ ሌባ እየመነተፈ ግላዊ እርካታን ብቻ ሚዛን ያደረገ እጅግ ፈጣኑን እና ነባራዊውን የሸቀጥ አለም የምናረጋጋበት፤በተመስጦ አሰላስለን ሃሳባችንን የምናስተላልፍበት ፖለቲካዊ ኃይላችን ብሎም ሰውን የምንጎበኝበት የልግስና ክዋኔያችን ነው፡፡የቴአትር ጥበብ!!!

አብይ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ተንኮታኩተው ከወደቁ በኋላ፤ አለምን እያስተዳደረ ያለው ወቅታዊው የአገዛዝ ዘዴ በየጊዜው እንደ እባብ አፈር እየላሰ ውድቀቱን እያደሰ ባለበት ተጨባጭ ሁኔታ፤ መጪውን ጊዜ እንዴት ማለም እንችላለን? በምን አግባብስ መመኘት ይሆንልናል? ምኞት እና ደህንነት ወቅቱ ያነገሳቸው ቅድመ-መስፈርቶች በሆኑበት አለም ውስጥ እንዴት ነጻ ውይይት

ማድረግ እንችላለን? የግል ክብራችንን ሳናስቀድም፣የራስ ጥቅማችንን የማጣት ፍርሃትን ወዲያ አሽቀንጥረን ጥለን እጅግ አደገኛ ድንበሮችን የመሻገር ወኔው አለን?

በዛሬው ጊዜ የመረጃ ፍጥነት ከእውቀት በላይ ተፈላጊነት አለው፡፡ መፈክሮች ከቃላት በላይ ዋጋ አላቸው፡፡የሙታን ምስሎች ከህያዋን አካል የበለጠ ይከበራሉ፡፡ በዚህ ሁሉ መሃል ሁላችንም ከስጋ እና ደም እንደተሰራን ሰውነታችንም ክብደት እንዳለው ለማስገንዘብ እና ለማስታወስ ቴአትር ዘብ ቆሟል፡፡ የስሜት ህዋሶቻችንን ካንቀላፉበት ሊያነቃ "በራሳችሁ ሽውራራ እይታ ብቻ አትጋረዱ" እያለ ሊነግረን ቴአትር ከእኛ ዘንድ አለ፡፡ቴአትር ምንጊዜም በመሃላችን አለ፡፡ የቃላትን ኃይል እና እውነተኛ ፍቺ ከፖለቲከኞች ምርኮ አስመልሶ ወደ ቀደመ ቦታቸው አኑሮ፣ ለሰብዓዊ ግልጋሎት ለማዋል ወደ ሃሳብ እና ሰላማዊ ክርክር ሜዳ ለማውረድ ወደ ምናልማት የህብረ-ራዕይ ከተማ ለመውሰድ.....ቴአትር ምንጊዜም አለ!

በታሪክ ነገራ እና የምናብ ኃይል ቴአትር አለምን መመልከቻ እና እርስ በርስ መተያያ የቅዳሜ ገበያችን፣ እንደ ቋጥኝ ከተጫነን ግድየለሽነት ውስጣችንን አጥርቶ፣ የጋራ እሴታችንን ሰብዓዊነትን የሚያንጸባርቅልን የፊት መስታወታችን ነው፡፡

ዜኖፎቢያ ንግግርን በተጠየፈበት፣ የነጭ የበላይነት ተመልሶ መንበሩን በተቆናጠጠበት፣ ከአመታት ትግል እና የሚሊየኖች መስዋዕትነት በኃላ ዛሬም ሰዎችን ተቀባይነት የሌላቸው ዜጎች እና በራሳቸው አይረቤነት እንዲሰማቸው ለማድረግ ቀን ከሌት በሚለፋበት፣ አፓርታይድ እና የፍትህ መዛባትን የተቃወሙ ታዳጊ ተባዕት እና እንስት በጠብ-መንጃ ጭንቅላታቸው በፈረሰበት፣ ያለ እድሜያቸው እስር ቤት በተወረወሩበት፣የአእምሮ መታወክ እና ቀኝ-ዘመም አክራሪነት ጥቂት የማይባሉ የሰለጠኑ ሀገራትን እየመሩ ባሉበት፣ስልጣንን በተቆጣጠሩ ኀልማሳ-ህጻናት መሪዎች መካከል እንደሚደረግ እቃቃ ጨዋታ የኒውክለር ጦርነት ስጋት በመላው አለም ባንዣበበበት፣ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ለጥቂቶች ብቻ ያለገደብ የተፈቀደ ሆኖ የማይጨበጥ ህልማቸውን ለማሳካት ሲሉ ከሰማይ የረዘሙ ግዙፍ አጥሮችን ለማለፍ ሲታገሉ በርካታ ስደተኞች የባህር ግብር የሚሆኑበት፣ በየዕለቱ ዳመና ተኳሽ፣ ሰው ጨራሽ ውድ ግንቦች በሚገነቡበት፣ .....ውጥንቅጥ በበዛበት አለም ውስጥ......መገናኛ ብዙሃን የግል እንጂ የህዝብ ርስት ባልሆኑበት.....የት ሄደን ነው ጥያቄያችንን የምናቀርበው?.....ማንን ነው አለማችንን መልሱልን ብለን የምንሞግተው?.....ከበረታን እና አንድ ከሆንን ቴአትርን ይዘን ስለ ሰብዓዊነት ቆም ብለን ማሰብ ብሎም አዲሱን ስርዓተ-ዓለም ማለም እንችላለን!!!!......ባለን ትልቅ ኃይል ተጠቅመን በመዋደድ እና ርህራሔ እንዲሁም በእውቀት እና በዓላማ ጽናት ባላጋራዎቻችንን ልንጋፈጥ ይገባናል፡፡

ከአረቡ አለም እንደመምጣቴ የኪነጥበብ ሰዎች በስራ ላይ የሚያጋጥሙንን ተግዳሮች ለመናገር እወዳለሁ፡፡በቅድሚያ ባላንጣዎቻችን ማፍረስ የሚፈልጓቸው ግምቦች በጉልህ የሚታያቸው የዚህ ትውልድ በሳል ቴአትር ሰሪዎች አባል በመሆኔ ክብር ይሰማኛል፡፡ከፊታችን እንደ ጅብራ ተጋርጠው አላሳልፍ ያሉን ግድግዳዎች ለችግራችን በጋራ እንድንቀሳቀስና ጭንቅላታችንን በእጥፍ እንድናሰራው አድርገውናል፡፡ግንቦቹ በምንሄድበት ቦታ ሁሉ በገጠር እና በከተማ፣ በመንደሮች እና በስደተኞች ካምፕ ሳይቀር ተመልካቾቻችንን እዛው እየፈጠርን፣ቴአትርን በምድር ቤት እና በጣራ ሰገነቶች ላይ፣በመኖሪያ ክፍሎች ውስጥ በጠባብ የህንጻ መተላለፊያዎች እና በአውራጎዳናዎች ላይ ለመስራት አስችለውናል፡፡ ማንኛውንም ነገር በራሳችን አውድ መልሰን የመስራት ባህሉን አዳብረናል፡፡ ሳንሱርን በመላ የምናስወግድበት ብልሃት፣የማናምንበትን ነገር የምንቃወምበት

መሳሪያችን ሆኗል ቴአትር፡፡ ዛሬ እነዚህ ግንቦች በመላው ዓለም ያሉ ቴአትረኞች ፊት ቆመዋል፡፡ የገንዘብ ኃይል መቼም ባያሳስበንም ፖለቲካዊ እውነታ ግን አዲሱ ሹም-ሳንሱር ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡

በመሆኑም ከመቼውም ጊዜ በላቀ አለምአቀፉ የቴአትር ማህበረሰብ እነዚህን  መልከ-ብዙ አንዴ በስውር ሲላቸው በገሃድ የሚገለጡ ግምቦችን ለመጋፈጥ አንድነቱን እና ቁርጠኝነቱን ሊያሳይ ይገባል፡፡ዛሬ የማህበራዊ እና የፖለቲካ መዋቅራችንን በጽናት እና በታማኝነት ዳግም በጥበብ መገንባት የሚያሻን አሳሳቢ ጊዜ ላይ ነን፡፡ ለምንገነባው ሰላማዊ የጥበብ አለም ችግሮቻችንን በመጋፈጥ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባናል፡፡

እንደመላው አለም ቴአትረኞች በየትኛውም ቅርጽ እውነትን ለዘላለም እንፈትሻታለን እንጂ ርዕዮተ-ዓለምን ወይም አንድ ሀይማኖትን አንከተልም፡፡ሁሌም የምንጠይቀው ሰብዓዊ ጥያቄያችን ጭቆናን የምንታገልበት ሰዋዊ ጥበባችን እስከመጨረሻው ይቀጥላል፡፡

እኛ ብዙ ነን! እኛ አንፈራም! ደግሞም እዚህ የምንቆየው ለመኖር ነው!

## የማያ ዘቢብ  አጭር ግለ-ታሪክ

ማያ-ዘቢብ  ሊባኖሳዊ የቴአትር አዘጋጅ፣ ጸሐፌ-ተውኔት እና የዙካክ ቴአትር  ድርጅት  መስራች  ነች፡፡ የፈጠራ ስራዎቿ በመካከለኛው ምስራቅ፣በአውሮፓ፣በዩናይትድስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣በአፍሪካ፣ በደቡብ አሜሪካ እና በደቡብ እስያ ለተመልካች ቀርበዋል፡፡ዘቢብ ቴአትርን በትምህርት ተቋማት እና በሁሉም ስፍራ በመላው ዓለም በማስተማር ትታወቃለች፡፡

የዘቢብን ሙያዊ ግልጋሎት ፈልገው አብረዋት ከሰሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የኪነ-ጥበብ ድርጅቶች መካከል ኤንዋይዩ አቡዳቢ ፐርፎርሚንግ አርትስ ሴንተር፣ሆስተን ዩኒቨርሲቲ ዊሊያምስ ኮሌጅ፣ክሬፌልድ/ሞንቼግላድባህ ሲቲ ቴአትር፣ሸዊንደልፈሪ ፌስቲቫል፣ሊፍት ፌስቲቫል እና ሮያል ኮርት ቴአትር ይጠቀሳሉ፡፡

ዘቢብ የ2007 የጎልድስሚዝ ለንደን ዩኒቨርሲቲ  እና የቼቨኒንግ ኬአርኤስኤፍ የቀድሞ ተማሪ፣ የ2010 የኢንተርናሽናል ካልቸራል ሊደርሺፕ አባል እና የ2010 የኒውዮርክ አይኤስፒኤ ፌሎውሺፕ አሸናፊ የነበረች ሲሆን የ2011 የሮሌክስ ሜንቶር ፕሮቴዤ አርትስ ኢንሼቲቭ የፒተር ሴላር ፕሮቴዤ በመሆን ተመርጣለች፡፡ ከሙያ አጋሮቿ ጋር የመሰረተችው ዙካክ የቴአትር ካምፓኒም አለምአቀፍ ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡

የ2012 የኢብሰን ስኮላርሺፕ እንዲሁም የ2014 አና ሊንድ ፋውንዴሽን ኢሮምድ ዲያሎግ ሽልማቶችን፣በማህበራዊ ዋስትና እና በፈጠራ ስራ ሲቀበል፤ ለወጣት ከያኒያን የሚበረከተውን የፕሪምየም ኢምፔሪያል ሽልማትን ከጃፓን የኪነ-ጥበብ ማህበር በ2017 እንዲሁም የኪራክ ፋውንዴሽን የባህል እና የሰላም ሽልማትን በተመሳሳይ አመት ለማሳካት ችሏል፡፡

ተርጓሚ - ምንያህል ተሾመ ቸሩ/ Translation : Menyahel Teshome Cheru

የቴአትር መምህር፣ ጸሐፊና ተዋናይ/ Lecturer, Theater Practitioner

ኢትዮጵያ/ Ethiopia